MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION
ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት
8221 Georgia Avenue, Silver Spring, MD. 20910
Tel: (202)-677-0094 Fax:
Web: http//www.moreshwegenie.org/

**ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት** **ቅዳሜ ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፪ሺህ፰ ዓ.ም.** **ቅፅ ፬ ፣ ቁጥር ፲፫**

# ለመላው የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያን በሙሉ፡-

# እንኳዋን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ!

ዓለምን የፈጠረ የዘለዓለም አምላካችን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በዚች ዕለት ግንዛቴን ፍቱልኝ፤ ድንጋዩንም ፈንቅሉልኝ ሳይል በባሕርይ ኃይሉ እና ስልጣኑ ሞትን ድል ነስቶ ተነስቷል። በእርግጥም አምላካችን በሞቱ ሞትን ገድሎ በትንሣኤው ሕይወትን ችሮናል እና ደስታ ይገባናል። የአምላካችን ወልድ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በረከት እና የውስጥ ነፃነት አይለየን። በዚች ቅዱስ ቀን ሊያዝን የሚገባው እግዚአብሔር አምላክ በአምሣያው የፈጠረውን እና የሚያከብረውን ሰው፥ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያለምንም ጥፋት እና ወንጀል በስግብግብነት እና በከንቱ ጥላቻ በመታወር እንደሙጃ የሚያጭደው እና የሚጨፈጭፈው የትግሬ-ወያኔ ቡድን ነው። በጌታችን እና በመድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የሚደነግጡትም ሆነ የሚታወኩት እነዚሁ በአጋንንት መንፈስ የሰከሩ እና በአራዊት ባሕርይ ያደጉት ከሃዲዎች ብቻ ናቸው። የተዘራው የሚታጭድበት ያች ጎደሎ ቀናቸው አይቀሬ ናትና በዕለተ ትንሣኤዋ ፊታችንን ወደፈጣሪያችን ማዞር ይጠበቅብናል። ኢትዮጵያም አጆቿን ወደ ኃያሉ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።

ይህ ግፈኛ የፋሽስት አገዛዝ በመላው ኢትዮጵያ ዜጋ ላይ የፈፀማው እና በመፈፀም ላይ የሚገኘው ግፍና በደል ተዘርዝሮ አያልቅም። «ዐማራው ጠላቴ ነው» በማለት ዘሩን ለማጥፋት እና ለማጽዳት የተነሳው ከ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ጀምሮ ሲሆን ዘመቻው ሊያባራ እና ሊገታ ባለመቻሉ፣ የመላውን የዐማራ ተወላጅ ልብ ሰብሮታል፤ ዝምታውንም አደፍርሶበት ይገኛል። የዚህን ዓመት የፋሲካ በዓል በምናከብርበት ወቅት በስጋት እና በፍርሃት የተወጠሩ ወገኖቻችንን ትጥቅ በማስፈታት ሌት ተቀን በመጨፈጨፍ ላይ ይገኛሉ። የወልቃይት፣ የጠገዴ፣ የጠለምት፣ የሠቲት እና ዋልድባ ወገኖቻችን ከተወለዱበት መንደራቸው ተፈናቅለው መድረሻ አጥተው ከግድያ የተርፉት በውክበትና በልቅሶ ላይ ናቸው። የጋምቤላ፣ የአፋር እና የኦሮሞ ኢትዮጵያውያን ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ህጻናት እና ሽማግሌዎች በትግሬ-ወያኔ ታጣቂዎች ያለምንም ርህራሄ በግፍ መጨፍጨፋቸው ተዘግቧል።እንዲሁም በሰሜን ኢትዮጵያ የሱዳን እስላማዊ አገዛዝ እና የትግሬ-ወያኔ በሚሠራው የፖለቲካ ቁማር ስሌት ታሪካዊ እና ለም መሬታችን ዐይናችን እያዩ ጆሮአችን እየሰማ በችሮታ ተሰጥቷል። ከዛሬ ፵(አርባ) ዓመታት በፊት አንድ ብር የማታወጣዋ አንድ ዶሮ ዛሬ ዋጋዋ ከመቶ ብሮች በልጧል፣ በ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. «500,000 ሺህ ኢትዮጵያውያን ተራቡ» ተብሎ አብዮት ሲፈነዳ ባለፉት ፳፭(ሃያ አምሥት) ዓመታት ግን በየዓመቱ በትንሹ ከ፳(ሃያ) ሚሊዮን የማያንሰው ሕዝባችን ለርሃብ ችግር ተጋልጦ ይገኛል። እንግዲህ በትግሬ-ወያኔ የአገዛዝ ዘመን የተገኘው «ዕድገት» ይህ ነው። ስለዚህ ይህ ሕዝብ የትንሣኤውን በዓል ትርጉም እና ዓላማ ለማንሰላሰል የሚችልበት አቅም የለውም። በአጠቃላይ «ትግራይን ከቀሪዋ ኢትዮጵያ ነፃ አወጣለሁ» በሚል ሰበብ አገር የሚያተራምሰው የትገሬ-ወያኔ ቡድን አገራችንን እንዳልነበረች አድረጎ በማፍረስ ጀግናውን ሕዝብ በባርነት ቀንበር ስር እንዲወድቅ አድርጎታል።

ውድ ኢትዮጵያን፡-

የኢትዮጵያ ትንሣኤ መቼ ነው? የንፁሀን ደም ይጮሃል! የትንሣኤው ነጻነት ያለው በእኛው በኢትዮጵያውያን እጅ እይደለንምን? ምድራችን በትግሬ-ወያኔ በግፍ የተጨፈጨፉ ከአምስት ሚሊዮን የማያንሱ የዐማራ ወንድሞቻችንን እና እህቶቻችንን ደም በውስጧ አምቃ በምጥ ላይ ትገኛለች። የግፉ እና የበደሉ ጽዋ ሞልቶ እየፈሰሰ ነው። ቅድስት አገራችን የሲዖል አምሣል ሆናለች። በአጭሩ በቁማችን ሞተናል፣ ተቀብረናል። ስለሆነም ትንሣኤ ያስፈልገናል። የመቃብራችንን ድንጋይ የሚፈነቅልልን በአንድነት የሚቀጣጠለው የሠፊው ኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣ ስለሆነ «አሁንስ በቃኝ» በማለት በኅብረት ለነጻነት የሚያበቃ ሕዝባዊ አመጽ እንዲነሳ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እና ሕዝቧን ይባርክ!**